ድምጽ አሰማን

# ድምጽ አሰማን

ድምጽ ስጠን እነድንጮህ ... ብርታት ስጠን የመንፈስ
በጩኸታችን ጥሪ.. በልቅሷችንም ብዛት... የኢያሪኮ ግንብ እንድፈርስ

ዝም አትበለን ጌታችን ... ዝም ብንልህ እኛ
ባንቀሰቅስህ ቀስቅሰን... እየተናወጽን ስንተኛ

ድምጽ ስጠን እንጩህ መርከቧን ሲመታት ማዕበል
እንድንቀሰቅስህ ቀስቅሰን  የዓለም ወጀብ ፀጥ እንድል

ድምጽ አሰማን..ብንሰማህ... ሳሙኤልን ልከህ ቀስቅሰን
ትቢያ ወድቀን እናልቅስ በለቅሷችን ብትምረን

በክብር ስትመጣ ያን ጊዜ...ተገልጸህ ጌታ በገሃድ
ሞተን እንዳንቀር... ዘለዓለም ተፈርዶብን የኃጢያት ፍርድ
ልብ ስጠን ልብ ብንል... ድምጽ አሰማን ብንነቃ
የሲኦል እሳት እንዳይበላን.. እንዳንጣል ከእሳት ሳንቃ

እንደምታውቀን እንወቅ ... ያኔ ከበለሷ ሥር
እንደምታየው እንረዳ ... የልባችንን ድብቅ ምሥጢር
እንደ አልዐዛር በጽናት... እንድንገባ ከአበው እቅፍ
ድምጽ አሰማን እንድንባንን... ከዓለም አልጋ ከሃጢያት እንቅልፍ

ከአይሁድ ምድጃ መታደም... ከእባብ ጋር ያለው ውይይት
የሃጥአን ድንካን ከለላ... የፈርኦንም ልዝብ ጣኦት
እንዳይማርከን ዘሬ... ከቤችን እንዳንወጣ
እንድበርድልን እሳቱ... የተቃጣው ያንተ ቁጣ
ጥራንና ድምጽ አሰማን... ስሙ በለን እንደገና
የዓለምን ሃጢያት ንቀው... እንደጸኑት እንድንጸና

የበረረው በግ ተመልሶ... የጠፋውም ድሪ ተገኝቶ
የኮበለለው ወንድማችን... የሪያ ዝምድናን ንቆ ትቶ
ሃሴት እንድሆን በቤችን...የበጉን ሥጋ እየበላን
ድምጽ አሰማን አምላካችን... እንድንሰማህ ስሙ በለን(2)

ወስበሀት ለእግዚአብሔር
ዮሴፍ አዱኛ ካሣዬ
ጥቅምት 25/ 2007